# የክርስቶስ ልደት ታህሳስ 29 ወይስ ዴሴምበር 25?

የእኛ ቤተ ክርስቲያን ልደትን ለምን ታኅሣሥ 29(28) ቀን ታከብራለች?ምዕራባውያንስ የልደትን በዓል ለምን December 25 ያከብራሉ? የጌታችን በዓለ ልደት መቼ ተጀመረ?መድኃኒታችን የተወለደበት ቀን ይታወቃልን?የልደት በዓል የሚከበርበትስ ቀን በምዕራባውያንና በእኛ ቤተ ክርስቲያን ለምን ተለያየ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን በመጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ካለመገለጹ የተነሣ ትክክለኛውን ቀን ለማግኘት ታሪክን ተከትለው ብዙ የደከሙ አሉ። ከዚሁም የተነሣ ዕለተ ልደቱን በተመለከተ የቀናት ልዩነቶች ተከሥተዋል።
ሆኖም ግን ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ቀኑን ይህ ነው ብሎ በግለጽ ባይናገርም አመልካቺ የሆነ ፍንጭ ሳይሰጥ ግን አልቀረም።
ይህንን ለመረዳት በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ አንድ ከቁጥር 8-14 የተጻፈውን መመልከት ያስፈልጋል።

“በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ። ሚስቱም ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች። ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበር። . . . እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት። በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር። የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፤ ፍርሃትም ወደቀበት። መልአኩም እንዲህ አለው፦ ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፣ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፣ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ተድላና ደስታም ይሆንልሃል፣ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።” /ሉቃ፩÷፭፣ ፰÷፲፬/

በዚህ ክፍለ ምንባብ በጣም አስፈላጊ የሆነ አመልካቺ (ጠቋሚ) ነገር ተመልክቶ እናገኛለን። ሆኖም ይህን አሳብ ፈልፍሎ ለማግኘት ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃልና አሳብ ጋር ተዛምዶ ሊብራራና ሊተረጎም ያስፈልገዋልና ነገሩን በጥንቃቄና በማስተዋል መከታተልን ይጠይቃል። ዋናው አመልካቺ ፍሬ ነገር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ያበሠረበት ቀን በዕብራውያን ዘንድ “በዓለ ሥርየት” ተብሎ ይከበር የነበረው ቀን መሆኑ ነው።በዓለ ሥርየት የሚባለው በዓል በዕብራውያን አቆጣጠር በሰባተኛው ወር ማለትም በታስሪን (ጥቅምት) አሥረኛ ቀን የሚውል ታላቅ በዓል ነበር። ይኸውም በዓል በኦሪት ሕግ “በሰባተኛው ወር፣ በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢአታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ። ታላቅ ሰንበት ይሆንላችኋል . . .” ተብሎ የታዘዘበት ታላቅ በዓል ነበር። /ዘሌ ፲፮÷፳፱—፴፤ ፳፫÷፳፯፤ ዘኍ ፳፱÷፯-፲፩/

በዚህ በዓል ቀን ሊቀ ካህናቱ የተቀደሰ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ወደ መቅደስ ይገባል። በእግዚአብሔር ፊት ባለው መሠዊያ የእሳት ፍህም አምጥቶ ጥናውን ይሞላል። እንዳይሞት የጢሱ ደመና በምስክሩ ላይ ያለው መክደኛ (ማስተሥረያ) ይሸፍን ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ ያደርጋል።እንዲሁም ካህኑ ለማስተሥረይ ወደ መቅደሱ በሚገባበት ጊዜ መጀመሪያ ለራሱ፣ ከዚያም ለሕዝቡ ሁሉ አስተሥርዮ እስኪወጣ ድረስ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሌላ ማንም ሰው አይኖርም ነበር። ዘሌዋ ፲፮÷፲፯። እንግዲህ ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ እነዚህ ድርጊቶች መፈጸማቸውን ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ገልጾአቸዋል። “እርሱም (ዘካርያስ) በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት። በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር።” ይላል። ስለዚህ ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበት ቀን የተጠቀሰው ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት በበዓለ ሥርየት ቀን ሲሆን ይህም በዕብራውያን አቆጣጠር በጥቅምት አሥረኛ ቀን ነው።
ስለዚህ ቅዱስ ሉቃስ ይህን ቀን በተለየ ሁኔታ ጌታችን ለተወለደበት ቀን ታሪካዊ የአኀዝ መነሻና የመሠረት ድንጋይ መሆኑን ጠቁሞ አመልክቶአል ማለት ነው። ይህ ዘካርያስ የተበሰረበት ቀን የአይሁድ በዓለ ሥርየት የዋለበት በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር ጥቅምት አሥረኛ ቀን መሆኑን ብዙ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች መተርጉማን ገልጸው እናገኛለን። ለምሳሌም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ-ወርቅና ማር ዮሐንስ ወንጌለ ሉቃስ ምዕራፍ አንድን ሲተረጉሙ ሰፋ ባለ ሐተታ ገልጸውት እናገኛለን። የኢትዮጵያ መተርጉማንም በተወራረሰ የሊቃውንት ትርጓሜ “ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ” ከሚለው ላይ በታሪክ ሲያትቱ “የጥቅምት ጨረቃ ሠረቀ ባደረገች በአሥር ቀን ነው፤ ዕለቱም ዕለተ ዮሴፍ (በዓለ ሥርየት) ነው፤. . . ተሰብስበው ይጸልያሉ፣ ወበይእቲ ዕለት አሕምምዋ ለነፍስክሙ (በዚያች ዕለት ራሳችሁን ታዋርዳላችሁ) እንዲል” ብለው አስረድተዋል። (ትርጓሜ ወንጌል፣ ገጽ 324) እስከዚህ ድረስ ዘካርያስ ዮሐንስን እስከሚወልድ የተበሠረበት ቀን በዓለ ሥርየት በሚባል በዕብራውያን አቆጣጠር ታስሪን (ጥቅምት) አሥር ቀን ለመሆኑ የተገናዘበበትን ትምህርታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ አይተናል። አሁን ደግሞ ይህን አቆጣጠር ከኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት እንደሆነና መቼ እንደሚያርፍ እንመልከት። በዕብራውያን አቆጣጠር በዓለ ሥርየት የዋለው በጨረቃ አቆጣጠር ጥቅምት አሥር ቀን ስለነበር ይህንን ወደ ኢትዮጵያውያን የቀን አቆጣጠር መልሶ ዕለቱን ለማግኘት ወደ ዘመን አቆጣጠር መግባት ግድ ይሆናል። ነገር ግን ወደዚህ የቀን አቆጣጠር ዝርዝር ብንገባ የያዝነውን ጉዳይ እንዳያወሳስበው ዝርዝር ሐተታውን ትተን እንዲሁ ዕለቱ የሚውልበትን ብቻ እንመልከት። በዕብራውያን አቆጣጠር ወርኀ ታስሪን (ጥቅምት) አሥር ቀን በኢትዮጵያ አቆጣጠር የዋለው መስከረም 27 ቀን ነበር። ይኸውም የጨረቃ የቀን አቆጣጠር ሲለወጥ የሚገኝ ነው።

ይህም ማለት በጨረቃ አቆጣጠር 10 ቀን የነበረው በዓለ ሠርቅ በፀሐይ የቀን አቆጣጠር መስከረም 27 ቀን ነበር ማለት ነው። ስለዚህ ዘካርያስ የተበሠረው መስከረም 27 ቀን ሆኖ እናገኘዋለን። በዓሉ ወዲያው እንዳበቃ ዘካርያስ ወደ ቤቱ ገባ፤ መጥምቁ ዮሐንስ ተፀነሠ።

ቅዱስ ወንጌል "የማገልገሉ ጊዜ ሲፈጸም ወደ ቤቱ ገባ። ሚስቱ ኤልሳቤጥም ፀነሠች" ሲል ያስረዳል። ቅዱስ ያሬድ ይህን መሠረት በማድረግ "ወእምድኅረ ክልዔ መዋዕል ፀንሠት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ ከሁለት ቀንም በኋላ ፀነሠች" ብሏል። ስለዚህ ዮሐንስ መጥምቅ የተፀነሠው መስከረም 29 ቀን ነው ማለት ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊና በፊቱ የሚሄድ መልእክተኛ መሆኑ በነቢያት ትንቢት ተነግሮ ቆይቷል። ኢሳ ፵÷፫-፭፤ ሚል ፫÷፩። እንደ ትንቢቱም ቃል ሁሉ ዮሐንስ ከፅንሠቱ ዕለት ጀምሮ በተፈለገው መንገድ ለጌታችን ኅዳናውን እያቀና የሚሄድ የፊቱ መልእክተኛ ሆኖ ተገኝቶአል። ሉቃ፩÷፳፮-፴፱። መጥምቁ ዮሐንስ የተፀነሠበትና ለተወለደበት ቀን ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው መነሻ አብነት ሆኖ ይገኛል ማለት ነው።እንግዲህ በዚህ ታሪካዊ ቁርጠኝነትና ትስስር መሠረት ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛ ወሯ ለዘካርያስ ያበሠረው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ተልኮ "ትፀንሻለሽ፣ ትወልጃለሽ" በማለት መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትፀነስና እንደምትወልድ ነገራት። ይህም መጥምቁ ዮሐንስ ከተፀነሰበት ጊዜ ፷፱ ቀን) አንሥቶ ሲቆጠር መጋቢት 29 ቀን ይሆናል።መልአኩ እመቤታችንን ሲያበስራት "መካን ትባል ለነበረችው (ለኤልሳቤጥ) ይህ ስድስተኛ ወር ነው" ሲል የተናገረው የፅንሰትዋን ጊዜ የሚያመለክት አይደለምን?ሉቃ 1÷36-38። ስለዚህ መጋቢት 29 ቀን ቃል ሥጋ የሆነበትና በድንግል ማኅፀን የተፀነሰበት ዕለት ነው ማለት ነው። ከዚህ ከመጋቢት 29 ቀን ጀምሮ ወንድ ልጅ በእናቱ ማኅፀን የሚቆይባቸውን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀናት (275 ቀናት) ስንቆጥር ጳጉሜን ጨምሮ ዕለተ ልደቱ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ላይ ይውላል።

ስለዚህም መጋቢት 29 ቀን የተፀነሰው ጌታችን ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ ፈጽሚልና ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በእናቱ ማኅፀን ቆይቶ ታኅሣሥ 29 ቀን በቤተልሔም ዘይሁዳ ተወለደ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክና የትውፊት ማስረጃዎችን መሠረት አድርጋ የመድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ታኅሣሥ 29 ቀን በታላቅ ምስጋና ታከብራለች።

ነገር ግን በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር, በ 3 ዓመት(ማለትም በሉቃስ ዘመን) ጳጉሜ 6 ስለምትሆን ለቀጣዩ ዓመት ማለትም በዮሃንስ ዘመን ልደት ታኅሳስ 28 ይሆናል::በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ 28 የሆነበት ምክንያትያለፍፈው ዓመት ዘመነ ሉቃስ ጳጉሜን 6 ነበር ጌታ ደግሞ የተፀነሰው መጋቢት 29 ቀን ነው ከዚያ ጀምሮ ያሉትን ቀናት ብንቆጥር እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን 275 ቀን ወይም 9 ወር ከ 5 ቀን ይሆናል ::

ስለሆነም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስርስትያን እና ሌሎችም ቤተ ክርስቲያናት በዓለ ልደትን ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የሚያከብሩት በተረዳና በታወቀ ማስረጃና መሠረት ላይ ተመሥርተው ነው እንጂ እንዲሁ አይደለም።

የዘመን መጀመሪያ የጌታችንና የመድሐኒታችን የልደት ቀን መሆን የለበትም ወይ ለምን መሰከረም ላይ ዘመን እንለውጣለን ?የሚል ጥያቄ እዚህ ላይ ሊነሳ ይችላል፦የኛ እንቁጣጣሽ የዓመተ ምህረት መለወጫ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የዘመን መለወጫ ነው! አውሮፓውያን የጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር የሚባለውን የሚከተሉ ሲሆን ይህ አቆጣጠር የዓመተ ምሕረት መለወጫ እንጂ እንደ እኛ ጠቅላላ የዘመን መለወጫ አይደለም።የኛ አዲስ አመት ግን ከክርስቶስ ልደት በፊትም ስንጠቀምበት የነበረ የዘመን መለወጫ ነው!

አውሮፓውያን የዓመተ ምህረት መለወጫ ቢሉም ግን እንደ ጠባዩ÷ እንደ አጠራሩና እንደ ፍላጎታቸው ልክ በመድኃኒታችን ልደት አልጀመሩም(ልደት የሚያከብሩት December 25 አዲስ አመታቸውን January 1 ነው..) የልደትን በዓል እንደ ቀን አቆጣጠራቸው ካከበሩ በኋላ እንደገና በስምንተኛው ቀን የዘመን መለወጫ ብለው ያከብራሉ። ይህም የጎርጎሮሳውያን የዘመን አቈጣጠር በክርስቶስ ልደት ላይ አለመመሥረቱን÷ ሌላ ጠባይ ወይም ሰው ሠራሽ ሥርዐት የተቀላቀለበት መሆኑን ያሳያል። ክርስትናን ተመርኩዞ ቢነሣ ኖሮ በእርግጥ የመድኃኒታችንን ልደት መነሻ አድርጎ ሊዘምት በተገባው ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን አሁንም ቢሆን የልደቱን በዓል ለብቻ አክብረው እንደገና ከሳምንት በኋላ የዘመን መለወጫ በዓልን ያከብራሉ።

የኛ የዘመን መለወጫ በዓል ግን ከሕገ ልቡና ቃል በቃል ተምረን÷ በኦሪት የመጽሐፍ መሠረት አግኝተንለት በወንጌልም አጽንተን ይዘነው የኖርነው ሦስት የሥራ ዘመን ክፍል የተላለፈና እዚህ የደረሰ ነው።

እኛ የዘመን መለወጫ(መስከረም 1) ብለን በሀገራችን ባህል የምናከብረው ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር የተገኘበት÷ ብርሃን÷ ጊዜ÷ ዕለት÷ ሰዓት የተፈጠሩበት፤ ለብርሃን÷ ለጊዜ÷ ለዕለት÷ ለወር ለዓመት ጥንት መሠረት የሆነ ቀን ነው። ይህንን ሁሉ በማስገኘት እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት÷ ዓለምን በመፍጠር ከሃሊነቱን ያረጋገጠበት ቀን ነው ብለን ነው የምናከብረው። ስለዚህም ጥንተ ብርሃን÷ ጥንተ ዕለት÷ ጥንተ ጊዜ÷ ጥንተ ፍጥረት ርእሰ ዐውደ ዓመት ብለን ነው የምናከብረው። በዚህ ስያሜ በዓሉ ርእሰ ዐውደ

ዓመት ይባላል!

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የምዕራባውያን የልደት በዓል ለምን December 25 ሆነ?